# ተሽሎክላኪዎች
(ከፍቅሬ ቶሎሳ)

በሽብር ነበልባል ውስጥ እጥፍጥፍ እያልን፣
እየተሽሎከለክን፣ እየተክልክልፍን፣
አንዲት የእሳት ምላስ ሳትልሰን፣
የአብዮት መብረቅን ፍንዳታም እያሳለፍን፣
የአመፅ አውሎው የዋሁን ሲመነጋግል፣
እኛ ለጥ ፀጥ ብለን፣
ነበልባል ውስጥ መሽገን እየተረፍን በግል፣
ብድግ፣ ብቅ እንላታለና ነበልባሉ ሲቀዘቅዝ፣
የሁከቱ ጥቅርሻማ ጠፈር ሲሆን ብራ፣
የአመፃው ቡልቃን ሲሰክን፣
የሽብሩ ሰማይ፣ አየር ብሩህ ሆኖ ሲጠራ፣
“አቤት! አለና! ዝግጁ ነን!”
እያልን፣ ከተፍ ነዋ ብንጠራ ባንጠራ።

ሞኝሞኙ፣ የዋህ የዋሁ ወዳድቆ፣
አለያም እዘብጥያ ወርዶ፣
ወይ ሲያልቅልን ተሰዶ፣
ወይ በሽብሩ ውስጥ ታርዶ፣
የተረፈው “ህሊና! ህሊና!”
እያለ ሲጮህ “ፍትህ! እውነት! ነፃነት!”
ስልጣንን ተጠይፎ እዳር ቆሞ ሲያስተውል፣
እኛ ጉብ ነዋ ከላይ፣ እየለፈፍን ስለሃርነት።

ውስጥ ውስጡን አድፍጠን፣
እናውቅበታለን ቆስቁሰን ገሩን ማነሳሳት፣
ደሙን ተረማምደን ስንሄድ ህሊና የለንም፣
የሚወቅሰን፣ ለሰው አናውቅም መሳሳት።
ጊዜውን ሰልለን፣ ውቅቱን አጥንተን፣
ተገንዝበን እየለካን የህብረተሰቡን ትኩሳት፣
ገርገሩን እየማገርን፣
ሲጋይ በአመፅ እሳት፣
እሱን እንደጧፍ እያነደድን፣
መንዝ ነው በውጋጋኑ ለህይወታችን እድሳት።

ቅን፣ ቅኑን እርካብ አርገን፣
እስልጣን ፈረስ ላይ ተፈናጠን፣
“ቼ! በለው!” ብለን መሽምጠጥ ነው
ሃቀኛውን በኮቴ ረጋግጠን።

የኛ ጩኸት እንዲመስል

የብዙሃኑን ጩኸት እይቀለብን፣
እናውቃለን ፀጥ ብለን ካደባንበት
መች ጩኸን መውጣት እንዳለብን።
ያንገታችን ሥር ቢፈነዳ አይታክተንም በሚዘዝ፣
አረፋ እስከምንደፍቅ አይሰለቸንም አተኻራ፣
መቶ ሺ ቶን እናወራለን
አንዲት ኪሎግራም ላንሰራ።

አፉን ዘግቶ እንደመቀመጥ
ሊያጋልጠን ቢቃጣ የህዝብ ተቆርቋሪ ነኝ ባይ
ወየውለት እሱን አያርገን
አለንና አጋላጭን ድባቅ የመምታት ፀባይ።

እንችልበታለን የህዝብን ቁጣ መቸርቸር፣
እናውቅበታለን በብዙሃኑ ስሜት መነገድ፣
ሙያችን ነው ደካማውን መጨፍልቅ፣
ጉልበታሙን በብልጠት ማስተናገድ።

አዳሜ ሲራኮት እንተርፋለን እኛ፣
ተርፈንም ወደፊት እንዘልቃለን፤
በማንኛውም ሥርዓትና ዘመን
እንደምን እንደምናሻቅብ ጠንቅቀን እናውቃለን።

ታጋዩ ገበሬ ፍዳ አይቶ
የዘራው ፍሬ ሲጎመራ
እኛ እንሰበስባለን አዝመራ፣
አይናችንን ሳናሽ ሳንፈራ።

ሁሉም ነገር የሚመቻቸው ለኛ ነው
ለኛ ነው የተሠራችው ይች ዓለም
"እውነት። ፍትህ። ነፃነት እያለ ለሚነደው
"ሃቀኛ"፣ በዚች ዓለም ስፍራ የለም።

(እ.ኤ.አ. ሐምሌ 15 ቀን 2006)
ሳንፍራንሲስኮ ካሊፎርንያ

www.ethiomedia.com